# በ COVID-19 ምክንያት ለከባድ ሕመም የመጋለጥ ከፍተኛ እድል ካለዎት ምን ማድረግ ይችላሉ?



## አሁን ባለን ግንዛቤ መሰረት በ COVID-19 ምክንያት ለከባድ ሕመም የመጋለጥ ከፍተኛ እድል ያላቸው ሰዎች የሚከተሉት ናቸው፡

- በዕድሜ የገፉ አዋቂዎች

**የሚከተሉት ያሉባቸው በማንኛውም ዕድሜ ላይ ያሉ ሰዎች፡**

- ካንሰር
- ስር የሰደደ የኩላሊት በሽታ
- COPD (ሥር የሰደደ የሳንባ እገዳ በሽታ)፣ አስም (ከመካከለኛ እስከ ከባድ)፣ ኢንተርስቲሺያል የሳንባ በሽታ፣ ሲስቲክ ፋይብሮሲስ እና የሳንባ የደም ግፊትን ጨምሮ ስር የሰደዱ የሳንባ በሽታዎች
- ከባድ የመርሳት ችግር ወይም ሌሎች የነርቭ ችግሮች
- የስኳር በሽታ (ዓይነት 1 እና ዓይነት 2)
- ዳውን ሲንድሮም
- ከባድ የልብ ችግሮች (ለምሳሌ፡ የልብ ስራ ማቆም፣ የልብ ደም ወሳጅ ቧንቧ በሽታ፣ ካርዲዮሚዮፓቲስ ወይም የደም ግፊት የመሳሰሉ)
- የኤች.አይ.ቪ ኢንፌክሽን
- የላላ በሽታ የመቋቋም አቅም ሁኔታ (የተዳከመ በሽታ ተከላካይ ስርዓት)
- የጉበት በሽታ
- ከመጠን በላይ ክብደት እና ከመጠን በላይ ውፍረት
- እርግዝና
- የሲክል ሴል በሽታ ወይም ታላሴሚያ
- ማጨስ፣ የአሁኑ ወይም የቀድሞ
- የጥጥር የአካል ክፍል ወይም የደም ስቴም ሴል ንቅለ ተከላ
- በአንጎል ውስጥ ያለውን የደም ፍሰትን የሚነካ ስትሮክ ወይም የአንጎል የደም ሥር በሽታ
- የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግሮች

ከታመሙ ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይደውሉ።

እራስዎን ለመጠበቅ ሊወስዱ ስለሚችሏቸው እርምጃዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ራስዎን እንዴት እንደሚጠብቁ የሚለውን የ CDC ጽሁፍ ይመልከቱ።

**cdc.gov/coronavirus**

324017-B June 15, 2021 3:01 PM

# እራስዎን እና ሌሎችን ለመጠበቅ እገዛ ያድርጉ፡



## ከጉዞ በፊት




**የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጎብኙ** እና የሕክምና መዝገብዎችዎን ያዘጋጁ።




**የ 12 ሳምንት** የመድኃኒት አቅርቦት ይቀበሉ።



የ COVID-19 **ክትባት** አማራጮችን ከጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ጋር ይወያዩ።



ከጉዞዎ በፊት ከ 3 ቀናት ባልበለጠ **የ COVID-19 ቫይረስ ምርመራ** ወይም ከ COVID-19 **መልሶ ማገገምን የሚገልጽ ሰነድ*** ያስፈልግዎታል።

*መልሶ ማገገምን የሚገልጹ ሰነዶች ባለፉት 3 ወራት ውስጥ ፖዘቲቭ የቫይረስ ምርመራ ማስረጃ እና ጉዞ ማድረግ እንደሚችሉ የሚገልጽ ከጤና እንክብካቤ አቅራቢ ወይም ከሕዝብ ጤና ባለሥልጣን የተላከ ደብዳቤ።



## በጉዞ ወቅት



**ክትባት ቢከተቡም** እንኳ አፍንጫዎን እና አፍዎን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍን እና ከፊት ጎኖች ጋር ጠበቅ አድርጎ የሚስማማ ማስክ ያድርጉ።



**እጆችዎን አዘውትረው ይታጠቡ** ወይም በውስጡ አልኮል ያለው የእጅ ማጽጃ ፈሳሽ ይጠቀሙ።




ከእርስዎ ጋር አብረው ከማይኖሩ ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪን ያስቀሩ (2 ሜትር/ 6 ጫማ)።



በጉዞ ወቅት ሕመም የሚሰማዎት ከሆነ ለ **IOM እና ለአየር መንገድ ሰራተኞች** ያሳውቁ።



## ከጉዞ ከተመለሱ በኋላ



በአካባቢዎ ለሚገኙ የተወሰኑ ግዴታዎች እና ምክሮች የመልሶ ማስፈር ኤጀንሲ ጉዳይ አማካሪዎን ያነጋግሩ።



**የ COVID-19 ምልክቶችን ይከታተሉ።** ሕመም ከተሰማዎት የሰውነትዎን የሙቀት መጠን ይለኩ።



እስካሁን ካልተከተቡ **የ COVID-19 ክትባት** ስለማግኘት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ወይም የመልሶ ማስፈር ኤጀንሲ ጉዳይ አማካሪዎን ያነጋግሩ።




ለ COVID-19 (የመጨረሻውን መጠንዎን ከወሰዱ 2 ሳምንታት) ሙሉ በሙሉ እስከሚከተቡ ድረስ "በጉዞ ወቅት" የሚለው ጽሁፍ ውስጥ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች ማከናወንዎን ይቀጥሉ።



## ከታመሙ እና COVID-19 ሊኖርብኝ ይችላል ብለው ካሰቡ፡



በቤት ውስጥ ይቆዩ። በተቻለ መጠን ከሌሎች ጋር አካላዊ ቅርርብን ያስቀሩ።



**የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን** እና **የመልሶ ማስፈር ኤጀንሲ ጉዳይ አማካሪን ያናግሩ።** የሕክምና አገልግሎት አቅራቢዎን ለማነጋገር አስተርጓሚ ከፈለጉ፣ የጉዳይ አማካሪዎ ሊረዳዎት ይችላል።




(የመተንፈስ ችግርን ጨምሮ) ድንገተኛ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ካሉብዎት ወደ 911 ይደውሉ እና ወዲያውኑ የሕክምና እርዳታ ይፈልጉ።

**cdc.gov/coronavirus**